


# የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ መንግስት

# የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር

## የተሻሻለው አካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የማማከር አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ

ህዳር 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ

# የተሻሻለው አካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የማማከር አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር.03/.2010

## መግቢያ

ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ በልማት እንቅስቃሴዎች ላይ የሚደረጉ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናቶች አካባቢያዊ፣ ማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ባገናዘበ መልኩ ማካሄድ አስፈላጊ በመሆኑ፤

የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አማካሪ ድርጅቶችና ባለሙያዎች ተገቢውን ሙያዊ ብቃትና የባለሙያ ስብጥር እንዲኖራቸው በማድረግ የህዝብንና የመንግስትን ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር ከፍተኛ ሀገራዊ ጠቀሜታ ያለው በመሆኑ፣

በአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የማማከር አገልግሎት የሚሰማሩትን ባለሙያዎች እና ድርጅቶች ብቁ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የሚያስችል መመዘኛ መስፈርት በማዘጋጀት ፈቃድ መስጠትና በተሠጠው ፈቃድ መሰረት አገልግሎት እየሠጡ መሆናቸውን መቆጣጠር አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የዜጎችን የአካባቢ መብቶች ሊያረጋግጥ የሚያስችል፣ ፍትሀዊ የንግድ ውድድር የሚያበረታታ፣ የሙያተኞችን ጥቅም የሚያሥጠብቅ፣ ወጥና በየደረጃው ሊተገበር የሚችል የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ፈቃድ አሰጣጥ ማዕቀፋዊ ስርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር 299/1995 ዓ.ም. አንቀጽ 7(2) እና አንቀጽ 20 መሰረት የወጣውን መመሪያ ቁጥር 02/2006 በመሻር ይህ መመሪያ ወጥቷል።

## ክፍል አንድ

## አጠቃላይ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “የተሻሻለው የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የማማከር አገልግሎት ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 03/2010” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

በዚህ መመሪያ ውስጥ ፡-

1/ “አመልካች" ማለት በአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የማማከር አገልግሎት ላይ በባለሙያነት ወይም በአማካሪ ድርጅትነት ለመመዝገብ ያመለከተ ሰው ነው፤

2/ “አማካሪ ድርጅት" ማለት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ለማከናወን በሚኒስቴር መስሪያቤቱ ፈቃድ የተሠጠው ህጋዊ ሰውነነት ያለው አካል ነው፤

3/ “ባለሙያ” ማለት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ የማማከር አገልግሎትን ለመስጠት በሚኒስቴር መስሪያቤቱ የሙያ ፈቃድ የተሠጠው ሰው ነው፤

4/ “የምስክር ወረቀት” ማለት የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ የማማከር አገልግሎት ለሚሰጡ ባለሙያዎች ወይም አማካሪ ድርጅቶች የሚሰጥ የብቃት ማረጋገጫ ነው፤

5/ “መዝገብ” ማለት በዚህ መመሪያ መሰረት በአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የማማከር አገልግሎትን ለመስጠት የተመዘገቡ ባለሙያዎች እና የአማካሪ ድርጅቶች መረጃ የያዘ ቋት ነው፤

6/ “የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት” ማለት አንድ ፕሮጀክት ወይም የመንግስት ሰነድ ተግባራዊ ሲሆን የሚያስከትለውን አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ውጤት በቅድሚያ ለይቶ በማወቅና በመመዘን፣ አዎንታዊ ውጤቶች የሚጎለብቱበት እንዲሁም በአካባቢያዊ፣ በማህበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ እና በባህላዊ ላይ ሊድርሱ የሚችሉትን አሉታዊ ተፅዕኖዎች ለማስወገድ፣ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል የታቀዱ እርምጃዎች የሚለዩበት ጥናት ነው፤

7/ “አግባብነት ያለው አካል” ማለት የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማን በሚመለከት የአማካሪዎችና ባለሙያዎች የብቃት ማረጋገጫ እና የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናትን የይሁንታ ፈቃድ እንዲሁም የቁጥጥር ስራዎችን እንዲያከናውን በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ እና አግባብነት ባላቸው ሌሎች ሕጎች ሥልጣን የተሰጠው አካል ነው፤

8/ “ሚኒስቴር” ወይም “ሚኒስትር” ማለት እንደየቅደም ተከተሉ የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፤

9/ “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

10/ ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለፀው አነጋገር ሴትንም ይጨምራል፡፡

## 3. የተፈፃሚነት ወሰን

1/ የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎች የአካባቢና ማህበረሰብ ተጽእኖ ግምገማ እና ስልታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የማማከር አገልግሎት ላይ በሚሰማሩ ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

## 4. ዓላማ

የዚህ መመሪያ ዋና ዓላማ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የማማከር አገልግሎት ላይ የሚሰማሩ ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች የብቃት ማረጋገጫ ለመስጠት የሚያሥችል መመዘኛ መስፈርት በማዘጋጀት ጥናቶች የአካባቢያዊ፣ የማህበራዊ እና የኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን በተሟላ መልኩ ያካተቱ እና ጥራታቸው የጠበቁ እንዲሆኑ ማስቻል ነው፡፡

## ክፍል ሁለት
## ተግባር እና ኃላፊነት

## 5. የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ተግባር እና ኃላፊነት

1/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማገኘት፣ ለማደስ ወይም ደረጃን ለማሻሻል የሚቀርቡ ማመልከቻዎችን ይቀበላል፤

2/ የቀረቡ ማመለከቻዎች መመሪያው በሚያዘው መስፈርት መሰረት ተሟልተው መቅረባቸውን እና ትክክለኛ መሆናቸውን በማረጋገጥ ለአመልካቹ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ይሠጣል፣ ያድሳል፣ ደረጃውን ያሻሽላል ወይም ማመልከቻውን ውድቅ እንዲሆን ይወስናል፤

3/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲመለስ ወይም እንደገና እንዲተካ የቀረበን ማመልከቻን በመመርመር እንዲመለስ ወይም እንዲተካ ይወስናል፤

4/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሠጠው ሰው የሙያ ስነ-ምግባር የሚጠይቀውን ግዴታዎች የማይወጣ፣ በሥራ አፈፃፀሙ የሙያ ብቃት የሌለው ወይም ተግባሩን በአግባቡ ያለከናወነ መሆኑ ሲረጋገጥ የምስክር ወረቀቱን ያግዳል ወይም ይሰርዛል፣

5/ ፈቃድ የተሠጣቸው ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶችን መረጃ የያዘ መዝገብ ወይም ቋት ያደረጃል፣ የተደረጉ ለውጦችን በመመዝገብ መዝገቡን ወቅታዊ ያደርጋል፣ለሚመለከታቸው አካላትም እንዲሠራጭ ያደርጋል፤

6/ ፈቃድ የተሠጣቸው ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶችን በመመሪያው መሰረት እየሠሩ ስለመሆኑ ክትትል ያደርጋል፤ያረጋግጣል፤

7/ ከአማካሪ ድርጅቶች የሚቀርቡ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ የሚሠሩ ባለሙያዎችን የሙያ ስብጥር እና ቁጥር ይገመግማል፣ ያፀድቃል፣

8/ የፈቃድ አሰጣጥ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን ይቀበላል፣ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ምላሽ ይሠጣል፤

9/የባለሙያዎች ወይም የአማካሪ ድርጅቶች ፈቃድ ለማገድ፣ለመሰረዝ፣ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እና ሌሎች ተያየዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በመመርመር ውሳኔ የሚሠጥ ኮሚቴ ያቋቁማል፡፡

## 6. የአማካሪ ድርጅቶች ተግባር እና ኃላፊነት

1/ ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የወሰደ አማካሪ ድርጅት በየጊዜው የተደረጉ የአድራሻና የባለሙያ ለውጦች እንዲመዘገቡለት ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በአንድ ወር ውስጥ ማሳወቅ አለበት፤

2/ በድርጅታቸው ውስጥ የሚሳተፉ ባለሙያዎች ህጋዊነታቸውን ማረጋገጥ አለባቸው፣

3/ አማካሪ ድርጅቶች የሚያዘጋጁቸው የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ የጥራት ደረጃ በጠበቀ ሁኔታ የመስራት ሃላፊነት አለባቸው፣

4/ በድርጅቱ የተሰሩና የፀደቁ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ እና የህዝብ ተሳትፎ ምክክር ቃለ ጉባዔ በአግባብ አደራጅተው ቢንያስ ለአስር ዓመት መያዝ አለባቸው፣

5/ አግባብነት ባለው አካል የክትትል ግምገማ በሚያደርግበት ወቅት መተባበር አለባቸው፣

6/ የተሰጠውን የብቃት ማረጋጋጫ ያለአግባብ የሚጠቀም አካል ከተገኘ ለሚመለከተው አካል የመጠቆም ሃላፊነት አለባቸው፣

7/ የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ሰነድ ከመካሄዱ በፊት የሚሳተፉ ባለሙያዎችን ለመወሰን የሚወጣውን ቢጋር ያዘጋጃል፡፡

## 7. የባለሙያዎች የአሰራር ስነምግባር ስርዓት

1) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት የሚያካሂዱ ባለሙያዎች የሚያከናውኗቸው ሙያዊ ስራዎች የአካባቢ ሕጎችን፣ የዘላቂ ልማት መርሆዎች እና የዚህ መመሪያ ድንጋጌዎችን መሰረት ያደረገ መሆን አለበት፤

2) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች በፖሊሲ፣ ፕሮግራም፣ ዕቅድና ፕሮጀክቶች ንድፍ ሃሳብ ዝግጅት ወቅት የአካባቢ ጉዳዮች እንዲካተቱ ማማከር ይጠበቅባቸዋል፤

3) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች የሚዛናዊነት፣ የፍትሀዊነት፣ የታማኝነት እና የተጠያቂነት መርሆችን በመከተል ስራዎች ማከናወን ይኖርባቸዋል፤

4) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች የግል ጥቅም ለማስጠበቅ ወይም የማይገባቸውን ጥቅም ለማግኘት የሌሎች ባለሙያዎችን ወይም ድርጅቶችን መልካም ስራዎችን ከማጣጣል ከማንቋሸሽ ወይም ከሌሎች ስጦታ ወይም ጉቦ በመቀበል፣ የተሳሳተ ወይም ማስረጃ የሌለው ቅሬታ ወይም ክስ በማቅረብ ወይም በሌላ ባልተረጋጠ ጥርጣሬ ላይ በተመሰረተ የሌሎችን ባለሙያዎች እና ድርጅቶች ዝና ከሚጎዱ እና የሥራ ዕድል ከሚያሳጣ ተግባራት መቆጠብ አለባቸው፤

5) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች በሙያ ስራዎቻቸው ሳይንሳዊ እውነታዎችን በመከተል ማከናወን አለባቸው፤

6) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች ራሳቸውን ከተሻሻሉ እና ከዘመኑ የአካባቢ ዳሰሳ አሰራሮች በማብቃት እነዚህን እውቀቶች ከሙያ ስራዎቻቸው ጋር ማዋሀድ ይጠበቅባቸዋል፤

7) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች የሥራቸውን ዓላማ ወይም ትክክለኛነትን የሚያስተጓጉል እንቅስቃሴዎች ለድርጅታቸው ወይም ለሚመለከተው ደንበኛቸው ማሳወቅ ይኖርባቸዋል፤

8) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች ሊገኙ የሚችሉ ታዓማኒ መረጃዎችን መጠቀም አለባቸው። ሆኖም ግን በቂና ታዓማኒ መረጃ ማግኘት ካልተቻለ ይህ እጥረት በጥናት ሰነዱ በማካተት በጥናቱ የተወሰዱ ግምቶች እና ውስንነታቸው፣ ለአካባቢው ያለው ጉዳት፣ የትንበያ አስተማማኝነት እና ለውሳኔ ሰጪው አካል ያለው እንድምታ በግልፅ ማስቀመጥ ይኖርባቸዋል፤

9) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች በጥናቱ ውስጥ ለተካተቱ ወይም ለተጠቀሱ ሃሳቦች ወይም ግኝቶች ሃላፊነት ይወስዳሉ፤

10) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች በቂ ልምድ ወይም የሙያ እውቀት ባልያዙበት ዘርፍ የሚያከናውኗቸው የሙያ ስራዎች በዘርፉ ልምድ እና እውቀት ካላቸው ባለሙያዎች በቅንጅት መስራት ይኖርባቸዋል።

11) የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ባለሙያዎች የሚሰጡትን የሙያ አገልግሎት በማጋነን ወይም ዋጋ በሚያሳጣ ሁኔታ ማስተዋወቅ እና ማከናወን የለበትም፡፡

## ክፍል ሦስት

## የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት አሰጣጥ

### 8. አዲስ የባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ በአካባቢ፣የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር በክልል እና በከተማ አስተዳደሮች አካባቢ ጥበቃ መ/ቤቶች እንዲሁም የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ግምገማ እንዲያካሂዱ ውክልና በተሰጣቸው የዘርፍ መስሪያ ቤቶች ውስጥ የማይሰራ ባለሙያ መሆን አለበት፡፡

2/ ማንኛውም አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት የሚፈልግ ሰው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት የሚከሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፤

ሀ) የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ወይም ፓስፖርት ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

ለ) ከሚያመለክተው የሥራ ዘርፍ ጋር ተያያዥነት ባለው መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ወይም ከውጪ ሀገር የተገኘ ከሆነ ከሚመለከተው አካል የተሰጠ የአቻ ግምት ማስረጃ እንዳለው የሚያረጋግጥ የትምህርት መስረጃ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

ሐ) ከጀማሪ አማካሪ በስተቀር በባለሙያው የተዘጋጁ አካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ዘገባዎችን የሚያሳይ ህጋዊ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

መ) አግባብነት ባለው የሙያ መስክ ቢያንስ የሁለት ዓመት የሥራ ልምድ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

ሠ) 3X4 የሆነ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤’

2/ በዚህ መመሪያ መስረት በአካባቢ ተፅዕኖ የሚሰማራ አማካሪ ባለሙያ ደረጃ በአዝል 1 በተዘረዘሩት ተፈላጊ መስፈርቶች መሰረት የሚወሰን ይሆናል፤

3/ በሙያው እንዳያገለግል የሚከለክል የሕግ እገዳ የሌለበት መሆን አለበት፤

## 9. የባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚፈልግ ማንኛውም ሰው በሚኒስቴርመስሪያ ቤቱ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት፣ የታደሠ የቀበሌ መታወቂያ፣ የቀድሞውን የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት በመያዝ መቅረብ አለበት፤

2/ ከሚሰራቸው ስራዎች የሚያገኙት ገቢ ግብር ስለመክፈሉ የሚያረጋግጥ ማስረጃ ማቅረብ አለበት፤

3/ የበላሙያ የምስክር ወረቀት ፈቃድ ከተሠጠበት ቀን ጀምሮ በየሦስት ዓመቱ ቀርቦ መታደስ አለበት፤

4/ የምስክር ወረቀት የእድሳት የጊዜ ገደብ ከማለፉ ከአንድ ወር በፊት ለማሳደስ ማቅረብ ይኖርበታል፤

5/ በተቀመጠው የጊዜ ገደብ የምስክር ወረቀቱን ያላሳደሰ ባለሙያ በሶስት ወራት ውስጥ በመቅረብ በቅጣት ይታደስለታል፣

6/ በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 5 መሰረት ፈቃዱን ያለሳደሰ ባለሙያ የምስክር ወረቀቱ እንደታገደ ይቆጠራል።

## 10. የባለሙያ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ደረጃን ለማሳደግ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

ማንኛውም የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማሳደግ የሚፈልግ ሰው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላት የሚከሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ አለበት፡-

1/ ማንኛውም ባለሙያ የደረጃ እድገት ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው የቀድሞ የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ከተሠጠው ከአንድ ዓመት በኋላ ነው፤

2/ የቀድሞን የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ማቅረብ አለበት፣

3/ ለመካከለኛ አማካሪነት ስርቶ ሰላጠናቀቃቸው ቢንያስ ሁለት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስራዎች ዝርዝር የሚገልፅ ደብዳቤ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

4/ ለከፍተኛ አማካሪነት ስርቶ ሰላጠናቀቃቸው ቢንያስ ሦስት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስራዎች ዝርዝር የሚገልፅ ደብዳቤ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

5/ 3X4 የሆነ ሁለት ጉርድ ፎቶ ግራፍ ።

## 11. በአማካሪ ድርጅት ስራ አስኪያጅነት ሆኖ ለመስራት መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች

1/ የአማካሪ ድርጅት ሥራ አስኪያጅ ሆኖ ለመስራት የሚፈልግ ሰው የሚከተሉትን መስፈርቶች ማሟላት አለበት።

ሀ) ከሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተሰጠ የባለሙያነት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት፤

ለ) በዚህ መመሪያ መሠረት ባለሙያው የሚያገኘው ደረጃ ቢያንስ የመካከለኛ አማካሪነት ደረጃ ሊኖረው ይገባል፡

## 12. አዲስ የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

1/ ማንኛውም አዲስ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው የሚፈልግ ሰው ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና የሚከሉትን መረጃዎች አያይዞ ማቅረብ ይኖርበታል፡-

ሀ) አማካሪ ድርጅት ለሚያመለክተው ደረጃ በዚህ መመሪያ በዕዝል 2 የተዘረዘሩትን የመመዘኛ መስፈርቶች አሟልቶ መገኘት ይኖርበታል፤

ለ) የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ጥያቄ ባቀረበው ድርጅት ስም በሚመለከተው አካል የተሠጠና የታደሰ የንግድ ፈቃድ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

ሐ) የመስክር ወረቀት እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀረበው ድርጅት ባለቤቶች ከአንድ ግለሰብ በላይ ከሆኑ ስልጣን ባለው አካል የፀደቀ የድርጅት መመስረቻ ሰነድ፣ መተዳደሪያ ደንብ  እና ማመልከቻውን ይዞ የቀረበው ግለሰብ የውክላና ማስረጃ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፤

መ) ከባለሙያዎችጋር የተደረገ የሥራ ውል ስምምነት ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

ሠ) የመስሪያ ቢሮ ያለው መሆኑን ማረጋገጫ ሰነድ ወይም ሕጋዊ የቤት ኪራይ ውል ከአንድ ፎቶ ኮፒ

ረ) የድርጅቱ ባለቤት ወይም ስራ አስኪያሄጅ 3X4 የሆነ ሁለት ፎቶ ግራፍ፡፡

2/ አዲስ የምስክር ወረቀት ለመረከብ የድርጅቱ ባለቤት ወይም ሥራ አስኪያጅ ወይም ሌላ ውክልና ያለው ሰው በግንባር መቅረብ አለበት

3/ የውጪ ሀገር አማካሪ ድርጅት በአካባቢና የማህበረሰብ ተጽዕኖ ጥናት የማማከር ተግባር ማከናወን የሚችለው በሀገሪቱ ውስጥ ፈቃድ ከተሠጠው አማካሪ ድርጅት የጋራ ጥምረት በመመስረት ብቻ ይሆናል፡፡

## 13. የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማሳደስ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደስ የሚፈልግ ድርጅት ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚሁ ተግባር ያዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና የሚከተሉትን መረጃዎች ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

1/ ከሚመለከተው የግብር ሰብሳቢ መስሪያ ቤት የዘመኑን ግብር መክፈሉን የሚያረጋግጥ ማስረጃ ወይም የታደሰ የንግድ ፈቃድ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

2/ የታደሰ የባለሙያዎች የሙያ ብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

3/ በቋሚነት በድረጅቱ ውስጥ እየሠሩ ያሉ ባለሙያዎች ለመጨረሻዎቹ ሦስት ወራት ደመወዝ የተከፈለበት ፔይሮል ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

4/ ከሥራ የተቀነሰ ወይም የተሰናበተ ነባር ባለሙያ ካለ ሌላ ባለሙያ የተተካበትን ወይም የተቀጠረበትን የውል ስምምነት ሰነድ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

## 14. <u>የአማካሪ ድርጅት የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ደረጃን ለማሳደግ መሟላት ስለሚገባቸው ቅድመ ሁኔታዎች</u>

የብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ለማሳደግ የሚቀርብ ጥያቄ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለዚሁ ተግባር የተዘጋጀውን ቅፅ በመሙላትና ከሚከተሉትን መረጃዎች ጋር ተያይዞ መቅረብ አለበት፡፡

1/ ማንኛውም አማካሪ ድርጅት የደረጃ እድገት ጥያቄ ሊያቀርብ የሚችለው የቀድሞ የአማካሪነት ደረጃ ከተሠጠው ከአንድ ዓመት በኂላ ነው፣

2/ ለጠየቀው ደረጃ በመመሪያው መሰረት የተጠቀሰውን ስፋት የሚያሟላ የመስሪያ ቦታ መኖሩን የሚያረጋግጥ የቤት ባለቤትነት ማስረጃ ወይም ህጋዊ የቤት ኪራይ ውል ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

3/ ጥያቄው የቀረበው በወኪል ከሆነ የውክልና ማስረጃና የታደሰ የቀበሌ መታወቂያ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር፣

4/ ለተጠየቀው ደረጃ በመመሪያው መሰረት እንዲሟሉ የሚፈልጉ ባለሙያዎች የታደሰ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ከአንድ ፎቶ ኮፒ ጋር

## 15. <u>የውጪ ሀገር ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች</u>

1/ አማከሪ ድርጅቶች

ሀ/ ማንኛውም የውጪ አማካሪ ድርጅቶች በማማከር አገልግሎት ላይ ለመሰማራት በሀገሪቱ ውስጥ ፈቃድ ከተሠጣቸው አማካሪ ድርጅቶች ጋር ጥምረት መመስረት ይጠበቅባቸዋል  እና

ለ) ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የሥራ ፈቃድ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፡፡

2/ ባለሙያዎች

ሀ) በዚህ መመሪያ መስረት ለባሙያ የተገለፁትን መመዘኛዎች ያሟላ መሆን አለበት:

ለ) ከሚመለከተው የመንግስት አካል የተሰጠ የሥራ ፈቃድ

ሐ) የትምህርት ዝግጅት አቻ ትርጉም ማቅረብ ይኖርበታል፣

መ) የአገልግሎት ዘመኑ ያላለፈ ፓስፖርት ማቅረብ አለባቸው፡፡

## 16. ስለ ምስክር ወረቀት አሰጣጥና ይዘት

1/ በዚህ መመሪያ ውስጥ የተዘረዘሩትን መመዘኛዎች ያሟላ አመልካች ከአምስት የሥራ ቀናት በማይበልጥ ጊዜ ውስጥ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት ይሰጠዋል፡፡

2/ በሚኒስትር መስሪያ ቤቱ የሚሠጥ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የሚከተሉትን መረጃዎች መያዝ አለበት፡-

ሀ/ የባለሙያውን/ የድርጅቱን ሙሉ ስም፤

ለ/ የሥራ አድራሻ/ አድራሻ፤

ሐ/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት የተሠጠበት የማማከር አገልግሎት ዘርፍ፤

መ/ የምስክር ወረቀቱ ደረጃ፤

ሠ/ የምስክር ወረቀቱ የተሠጠበት ቀን፤

ረ/ የምስክር ወረቀቱ ፀንቶ የሚቆይበት የጊዜ ገደብ፤

ሰ/ የባለሙያውን ፎቶ ግራፍ/ የድርጅቱን ባለቤ ወይም ሥራ አስኪያጅ ፍቶ ግራፍ

## 17. የጠፋ ወይም የተበላሸ የምስክር ወረቀትን ስለመተካት

1/ የምስክር ወረቀቱ ዋና ቅጂ ከጠፋ ወይም ከተበላሸ አመልካቹ ለዚሁ ተግባር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተዘጋጀ ቅፅ ሞልቶ በምትኩ ሌላ የምስክር ወረቀት እንዲሰጠው ሚኒስቴር መ/ቤቱን መጠየቅ ይችላል፤

2/ የጠፋ የምስክር ወረቀትን ለመተካት ከሚቀርብ ማመልከቻ ጋር አግባብ ካለው የሕግ አስፈፃሚ አካል ምስክር ወረቀቱ መጥፋቱን የሚያረጋግጥ ህጋዊ ማስረጃ መያያዝ አለበት፤

3/ የምስክር ወረቀቱ መጥፋቱ ከተረጋገጠ በምትኩ ሌላ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤ሆኖም የተወሰነውን የክፍያ መጠን መፈፀም ይኖርበታል፤

4/ የተበላሸ የምስክር ወረቀት እንዲተካለት የተበላሸውን ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል፡፡

## 18. ማመልከቻ ውድቅ ስለማድረግ

ለምዝገባ የቀረበ ማመልከቻ ከሚከተሉት ምክንያቶች በአንዱ ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡ ይኸውም አመልካቹ፡-

1/ በአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ወይም በዚህ መመሪያ ውስጥ የተደነገጉ መስፈርቶችን የማያሟላ ከሆነ፤

2/ ስልጣን ባለው ፍርድ ቤት ችሎታ የሌለው ወይም ስራውን መስራት የማይችል መሆኑን ከተወሰነ ማመልከቻው ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

3/ በሥራው ሂደት የሥነ ምግባር ጥሰት ወይም ከሙያ አግባብ ውጪ የሥራው ተግባር በፈቃድ ሰጪው አካል መኖሩ ሰረጋገጥ

## 19. የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ስለማገድ

1/ የብቃት ማረጋገጫ የመስክር ወረቀት ሊታገድ የሚችለው የሚከተሉት ሁኔታዎች መፈፀማቸውን ሲረጋገጥ ይሆናል፤

ሀ) ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት ሙያው የሚጠይቀውን ሥነ-ምግባር በመጣስ ስራውን ተገቢ ባልሆነ አሠራር ያከነወነ ሲሆን፤

ለ) ለሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እንዲቀርቡ የሚጠየቁ ሪፖርቶች ወይም መረጃዎች ሳይቀርቡ ሲቀሩ፤

ሐ) የሌላ ሰውን ስራ የራሱ አስመስሎ የቀዳ ወይም የገለበጠ እንደሆነ፤

መ) ከሚኒስቴሩ ወይም አግባብነት ካለው አካል ይሁንታ ሳያገኝ በአንድ ሰነድ ዝግጅት ከአንድ መስክ በላይ ከተሠማራ፣

ሠ) በዚህ መመሪያ የተጠቀሱ ግዴታና ሃላፊነቶች ሳይወጣ ሲቀር፤

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑሥ አንቀፅ 1 መሠረት ጥፋተኛ ሆኖ የተገኘ ሰው ወይም ድርጅት ላይ የእገዳ እርምጃው የሚቆየው እንደ ጉዳዩ ሁኔታ ከ2 ዓመት ላልበለጠ ጊዜ ይሆናል።

3/ እገዳው ሊነሳ የሚችለው በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 የተጠቀሱትን ጉድለቶች በዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ 2 በተመለከተው ጊዜ ውስጥ መስተካከላቸው ወይም ሊታረሙ የሚችሉ መሆናቸውን በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ ይሆናል።

4/ የምስክር ወረቀቱን ያሳገዱ ምክንያቶች እገዳው በተጣለ በ2 ዓመት ጊዜ ውስጥ ካልተስተካከሉ ወይም በሚመለከተው አካል እገዳው እንዳይነሳ ሲወሰን የምስክር ወረቀቱ ይሰረዛል።

## 20. የምስክር ወረቀት ስለመሰረዝ

1/ የምስክር ወረቀት ከዚህ በታች በተጠቀሱት ምክንያቶች መሰረት ይሰረዛል።

ሀ) ምስክር ወረቀት የተሰጠው ባለሙያ ከዚህ ዓለም በሞት ሲለይ ወይም በራሱ ጥያቄ ወይም በሌላ ምክንያት ስራውን ሲተው

ለ) አመልካቹ የምስክር ወረቀቱን ያገኘው በማጭበርበር መሆኑ ከተረጋገጠ፣

ሐ) የምስክር ወረቀቱ ከህግ አግባብ ውጪ ለሌላ ሰው ተላልፎ ከተገኘ፣

መ) የምስክር ወረቀት የተሰጠው ድርጅት መክሰሩ ወይም መፍረሱ አግባብነት ባለው ፍርድ ቤት ሲረጋገጥ ወይም በራሱ ምክንያት ስራውን አቁሞ የምስክር ወረቀቱን ሲመልስ

ሠ/ አመልካቹ ከብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀቱ ዓላማዎች ጋር የሚቃረኑ ተግባራትን ሲያከናውን ከተገኘ

ረ) ፈቃድ ባላገኘበት የማማከር ደረጃ ተሰማርቶ ከተገኘ

2/ በዚህ አንቀጽ መሰረት የምስክር ወረቀቱ የተሰረዘበት ማንኛውም ሰው የምስክር ወረቀቱን በአስር ቀናት ውስጥ የመመለስ ግዴታ አለበት፡፡

21. ስለ ቅሬታ አቀራረብ

1/ የብቃት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀት ለማውጣት ወይም ለማሳደስ ወይም ለማሳደግ የቀረበ ማመልከቻ በሚኒስቴር መስሪያ ውድቅ በመደረጉ ወይም የምስክር ወረቀቱ በመሰረዙ ወይም አይሻሻልም በመባሉወይም በማናቸውም ምክንያት ማመልከቻው ውድቅ በመደረጉ ቅር የተሰኘ አመልካች ሁኔታው በጽሁፍ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ በ5 የስራ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም ለሚመለከተው ባለስልጣን መ/ቤት በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የቀረበውን ቅሬታ በመመርመር የፈቃድ ሰጪው አካል ውሳኔውን በ5የስራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

3/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 2 መሰረት በተሰጠው ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ያለውን ቅሬታ በ3 የስራ ቀናት ውስጥ ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብነት ላለው መ/ቤት የበላይ ሀላፊ ቅሬታውን በጽሁፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

4/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 3 መሰረት ቅሬታ የቀረበለት መስሪያ ቤቱ የበላይ ሀላፊም የቀረበውን ቅሬታ በመመርመር ውሳኔውን በ10 የስራ ቀናት ውስጥ ለአመልካቹ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

5/ የመ/ቤቱ የበላይ ሀላፊ በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ አመልካች ቅሬታውን ለሚመለከተው መደበኛ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

6/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ1እና 3 ላይ የተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ቅሬታውን ያላቀረበ አመልካች የተወሰነውን ውሳኔ እንደተቀበለ ይቆጠራል፡፡ ሆኖም ቅሬታውን ሊያቀርብ ያልቻለው ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መሆኑ በበቂ ህጋዊ ማስረጃ ከተረጋገጠ ማመልከቻው ተቀባይነት ይኖረዋል፡፡

22. ስለውክልና

1/ አዲስ ወይም ምትክ የምስክር ወረቀት እንዲሰጥ እነዲሁም እንዲታደስ ወይም የደረጃ እድገት እንዲደረግ የሚቀርብ ጥያቄን ከምስክር ወረቀት ያዡ በተሰጠ ህጋዊ ውክልና ካልሆነ በስተቀር ማስፈፀም አይቻልም፡፡

## 23. የአገልግሎት ክፍያ

1/ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ወይም አግባብነት ያለው አካል ለአማካሪ ባለሙያና ለአማካሪና ድርጅት ለሚሰጠው አገልግሎት የሚከተለውን የክፍያ መጠን ያስከፈላል፡፡

| ተ.ቁ | የክፍያ ምንክያት | ለአዲስ ፍቃድ | ለፍቃድ እድሳት | የጠፋን ለመተካት | ደረጃን ለማሳደግ |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ለባለሙያ | 300 | 150 | 200 | 250 |
| 2 | ለአማካሪ ድርጅት | 500 | 300 | 350 | 400 |

2/ የክፍያ ስርዓቱ በሚኒስትሮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተግባራዊ ይሆናል፡፡

## 24. የባለሙያዎች እና የአማካሪ ድርጅቶች ተሳትፎ

1/ አንድ ባለሙያ በመመሪያው የተዘረዘሩትን መስፈርቶች በማሟላት ከሁለት የሙያ ዘርፎች በላይ ፈቃድ ሊወስድ አይችልም፡፡

2/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 1 እንደተጠበቀ ሆኖ አንድ ባለሙያ በአንድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት ላይ በአንድ አማካሪ ድርጅት ውስጥ ሊሳተፍ የሚችለው በአንዱ የሙያ ፈቃድ ብቻ ነው፡፡

3/ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ 2 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ነገር ግን በአማካሪው ድርጅት በቀረበው ቢጋር መሰረት እና በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ወይም አግባብነት ባለው አካል ይሁንታ ሲሰጠው በሁለት ዘርፍ ላይ በአንድ የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ሊሰራ ይችላል ፡፡

4/ ማንኛውም ባለሙያ ሁለት ፈቃድ ካለው በሁለት አማካሪ ድርጅት ውስጥ በዋና (መስራች) አባልነት ሊመዘገብ ይችላል፡፡

## ክፍል አራት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**25. መመሪያውን ስለማሻሻል**

ሚኒስቴሩ ይህን መመሪያ እንደ አስፈላጊነቱ በማንኛውም ጊዜ ሊያሻሽል ይችላል::

**26. መሸጋገሪያ ደንጋጌ**

1/ ይህ መመሪያ ከመውጣቱ በፊት ተመዝግበው የብቃት ማረጋገጫ የተሠጣቸው ባለሙያዎች እና አማካሪ ድርጅቶች ይህ መመሪያ በፀደቀ በስድስት ወር ውስጥ በመመሪያው መሰረት መመዝገብ ይኖርባቸዋል ።

**27. የተሻሩና ተፈፃሚነት የሌላቸው ህጎች**

1/ በአካባቢ ዘርፍ የአካባቢ ተጽዕኖ ፣ የአካባቢ ኦዲት እና የአየር ንብረት ለውጥ ጥናት የማማከር አገልግሎት የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ምስክር ወረቀት አሰጣጥ መመሪያ ቁጥር 2/2006 በዚህ መመሪያ ተሽሯል ።

**28. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ መመሪያ...ኅዳር 22... ቀን 2010 ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል ።

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

22/03/10

ገመዶ ዳሌ (ዶ/ር)

የአካባቢ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር

ሚኒስትር

ዕዝል 1፡ የአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አገልግሎት የሚሰጡ አማካሪ ባለሙያዎች መስፈርት

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የአካባቢ ዘርፍ ጉዳዮች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| 1 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ ኢኮኖሚያ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በኢኮኖሚክስ፣ ኢንቫሮንመንታል ኢኮኖሚክስ፣ አግሪካልቸርራል ኢኮኖሚክስ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>ለሁለተኛ ድግሪ፡ 1<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 0 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በኢኮኖሚክስ፣ ኢንቫሮንመንታል ኢኮኖሚክስ፣ አግሪካልቸርራል ኢኮኖሚክስ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በኢኮኖሚክስ፣ ኢንቫሮንመንታል ኢኮኖሚክስ፣ አግሪካልቸርራል ኢኮኖሚክስ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| 2 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ የማህበራዊ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በሶሾሎጂ፣ በሶሻል ስተዲስ፣ ሶሻል ዎርክስ፣ ሶሻል አንትሮፖሊጂ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 1<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 0 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በሶሾሎጂ፣ በሶሻል ስተዲስ፣ ሶሻል ዎርክስ፣ ሶሻል አንትሮፖሊጂ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በሶሾሎጂ፣ በሶሻል ስተዲስ፣ ሶሻል ዎርክስ፣ ሶሻል አንትሮፖሊጂ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| 3 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ የአካባቢ ጤና ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በአካባቢ ጤና፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 1<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 0 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በአካባቢ ጤና፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በአካባቢ ጤና፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ የሥራ አካባቢ ጤንነትና ደህንነት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| 4 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የብዝሐ ሕይወት እና የስርዓተ-ምህዳር ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በብዝሃ ሕይወት፣ በደን/ዱር እንስሳት/ በሥነ-ሕይወት በእጽዋት /በአግሮኖሚ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 1<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 0 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በብዝሃ ሕይወት፣ ስነ-ምህዳር በደን/ዱር እንስሳት/ በሥነሕይወት በእጽዋት ሳይንስ /በአግሮኖሚ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | ከፍተኛ | በብዝሃ ሕይወት፣ ስነ-ምህዳር በደን/ዱር እንስሳት/ | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8 |

| ተ.ቁ | የብቃት ማረጋገጫ የሚሰጥባቸው የአካባቢ ዘርፍ ጉዳዮች | የሚሰጠው የብቃት ደረጃ | የትምህርት ደረጃ | አግባብነት ያለው የሥራ ልምድ (በአመት) |
|---|---|---|---|---|
| | | አማካሪ | በሥነሕይወት በእጽዋት ሳይንስ /በአግሮኖሚ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| 5 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት የውሃ ሀብት አጠቃቀም አጥኚ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በውሃ ሀብት አጠቃቀም፣ ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የውሃ ምህንድስና፣ የከርሰ ምድር ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 1<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 0 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በውሃ ሀብት አጠቃቀም፣ ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የውሃ ምህንድስና፣ የከርሰ ምድር ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በውሃ ሀብት አጠቃቀም፣ ተፈጥሮ ሃብት አያያዝ፣ የውሃ ምህንድስና፣ የከርሰ ምድር ጥናት ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| 6 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ የአካባቢ ብክለት ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በአካባቢ መሀንዲስ ፣ ኬሚካል መሃንዲስ፣ በአካባቢ አያያዝ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 1<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 0 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በአካባቢ መሀንዲስ ፣ ኬሚካል መሃንዲስ፣ በአካባቢ አያያዝ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በአካባቢ መሀንዲስ ፣ ኬሚካል መሃንዲስ፣ በአካባቢ አያያዝ፣ በአካባቢ ሳይንስ፣ ኬሚስትሪ ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |
| 7 | በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘርፍ የሙቀት አማቂ ጋዝ ልቀት ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | በአየር ንብረት ለውጥ፣ በኬሚስትሪ፣ በአካባቢ ሳይንስ በአካባቢ ጤና ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 2<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 1<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 0 |
| | | መካከለኛ አማካሪ | በአየር ንብረት ለውጥ፣ በኬሚስትሪ፣ በአካባቢ ሳይንስ በአካባቢ ጤና ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 5<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 3<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 1 |
| | | ከፍተኛ አማካሪ | በአየር ንብረት ለውጥ፣ በኬሚስትሪ፣ በአካባቢ ሳይንስ በአካባቢ ጤና ወይም ተመሳሳይ መስክ ቢያንስ የመጀመሪያ ድግሪ ያለው | • ለመጀመሪያ ድግሪ፡ 8<br>• ለሁለተኛ ድግሪ፡ 5<br>• ለዶክተሬት ድግሪ፡ 3 |

የአካባቢ፣ የደንና የአየር ንብረት ለውጥ ሚኒስቴር ★ Ministry of Environment, Forest & Climate Change

## እዝል 2: *በአካባቢና የማህበረሰብ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናት አገልግሎት የሚሰጡ አማካሪ ድርጅቶች መስፈርት*

| ተ.ቁ | ለአማካሪው ድርጅት የሚሰጠው ደረጃ | አማካሪው ድርጅት የሚያስፈልጉት ባለሙያዎች | | | የሚስማራባቸው የአካባቢና ማህበረሰብ ተፅዕኖ ጥናት መስኮች | ሌሎች መስፈርቶች |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝርዝር | የሙያ ደረጃ | ብዛት | | |
| 1 | I | የኢኮኖሚያ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | መካከለኛ አማካካሪ | 1 | ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸው ፕሮጅክቶች እና ስክኬጂውል 1 ውስጥ የተካተቱ ፕሮጅክቶች ዝርዝር የሚያከናውን<br><br>በስኬጀውሉ ያልተካቱት ፕሮጅክቶች ዝርዝር በሥክሪንግን ፕሮጀክቱ ሊካተት የሚችልብትን ስኬጀውል በጥናት የሚለይ ይሆናል | ስራ አስኪያጁን ጨምሮ ቢያንስ ሁለት ቋሚ ሰራተኞች<br><br>መነሻ ካፒታል ቢያንስ 200 ሺ ብር<br><br>የመስሪያ ቦታ/ቢሮ ቢያንስ 30 ካሬ ሜትር<br><br>የቢሮ የጽህፈት መሳሪያዎች/ኮምፒዩተሮች |
| | | የማህበራዊ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የአካባቢ ጤና ተንታኝ ባለሙያ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የሙቀት አማቂ የጋዝ ልቀት ተንታኝ ባለሙያ | መካከለኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የብዝሐ ሕይወት እና የስርዓተ-ምህዳር ተንታኝ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የውሃ ሀብት አጠቃቀም ተንታኝ ባለሙያ | መካከለኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የአካባቢ ብክለት ተንታኝ ባለሙያ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |
| 2 | II | የኢኮኖሚያ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | 1 | ከስኬጀውል ሁለት ያሉትን ፕሮጀክቶችን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ጥናትን ያከናውናል | ስራ አስኪያጁን ጨምሮ ቢያንስ ሁለት ቋሚ ሰራተኞች<br><br>መነሻ ካፒታል ቢያንስ 150 ሺ ብር<br><br>የመስሪያ ቦታ/ቢሮ ቢያንስ 20 ካሬ ሜትር<br><br>የቢሮ የጽህፈት መሳሪያዎች/ኮምፒዩተሮች |
| | | የማህበራዊ ጉዳዮች ተንታኝ ባለሙያ | መካከለኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የአካባቢ ጤና ተንታኝ ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | 1 | | |
| | | የብዝሐ ሕይወት እና የስርዓተ-ምህዳር ተንታኝ | መካከለኛ አማካሪ | 1 | | |
| | | የውሃ ሀብት አጠቃቀም ባለሙያ | ጀማሪ አማካሪ | 1 | | |
| | | የአካባቢ ብክለት ተንታኝ ባለሙያ | ከፍተኛ አማካሪ | 1 | | |